ቁጥር፡- አ1162/11/ቮ4ሯ6

ቀን 1 0 2017

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ለጋምቤላ ህዝብ ነፃነት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጋህነዴን)

ጋምቤላ

የጋምቤላ ህዝብ ነፃነት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጋህነዴን) ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ግንቦት 10/2016 ዓ/ም በጋምቤላ ከተማ ቅዱስ ዮሴፍ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን አዳራሽ አካሂዶ ሪፖርት ቀርቧል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የካቲት 07 ቀን 2017 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ፓርቲው ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ፤ የታዛቢዎችን ሪፖርትና የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ ከአዋጅ ቁጥር 1162/11 አንፃር መርምሯል።

ፓርቲው የጠቅላላ ጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ለቦርዱ ገቢ ያደረገ ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤው ላይ 237 የፓርቲው አባላት የተገኙ መሆናቸውን እንዲሁም የፓርቲው አመራሮች ምርጫው ግልፅና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል።

ይሁንና ከቦርዱ ታዛቢዎች ሪፖርት መረዳት እንደሚቻለው በእለቱ በጠቅላላ ጉባኤው ላይ የተገኙት የፓርቲው አባላት በአጠቃላይ 171 የነበሩ ሲሆን ፤ይህም በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ዓ/ም አንቀጽ 74/1/ሰ እና በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 17(6) አንፃር በጠቅላላ ጉባኤው ላይ መገኘት ያለባቸው የአባላት ቁጥር 200 ከመሆኑ አንፃር ፓርቲው ጉባኤውን ያደረገው ባልተሟላ ምላተ ጉባኤ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በተጨማሪም የፓርቲው አመራሮች ምርጫ እጅ በማውጣት የተደረገ ሲሆን ይህም በአዋጁ ቁጥር 1162/2011 ዓ/ም አንቀጽ 74/3/ መሰረት ምርጫው በጉባኤው ታሳታፊዎች በሚስጥር ያለመካነወኑን የቦርዱ ታዛቢዎች ካቀረቡት ሪፖርት መረዳት ተችሏል።

በመሆኑም ፓርቲው ያደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ውድቅ የተደረገ ሲሆን ፓርቲው በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤውን በድጋሚ እንዲያደርግ ቦርዱ በአክብሮት ያሳስባል።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ም/ሰብሳቢ
National Electoral Board

ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ቦርድ — የፖለቲካ ፓርቲዎች

ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

CamScanner